# ኢትዮሚዲያ

## ርእሰ አንቀጽ

(ትርጉም መላኩ ፀጋዬ መኮንን እና ጓደኛው)

# የወንጀለኞች 'መንግስት' እና የህዝቡ ፈተና

-----------------------------------------------

ከቀናት በፊት ሴናተር ሩዝ ፌንጎልድ የአሜሪካ ምክር ቤት አባልና የአፍሪካ ንዑስ ኮሚቴ ሊቀመንበር የአፍሪካን ቀንድ አስምልክቶ ባደረጉት ንግግር የአፍሪካ ቀንድ "ለዓለም አቀፍ ጉርብትና በጣም የጎረበጠና አስቸጋሪ" ሲሉ ከገለፁ በኃላ በአዲስ አበባ የሚገኙትን የግዛቱ መሪዎች ተግባር ለመግልፅ የአሜሪካው ሸንጎ ምክር ቤት አባል ክሪስ እስሚዝ ከፊሪጁት አባባል ጋር በመስማማት ብቃት የሌለው መንግስት፣ የዘር ማጥፋት አገዛዝ፡ እኔ ያልኩብ ብቻ ይህን ባይ መንግስት መሆኑን በመግልፅ ሀገሪቱ አስፈሪ ወደ ሆነ ችግር በማምራት ላይ ያለች ሲሊ ስጋታቸውን ገልጠዋል። አገዛዙ ነብስ በማጥፋት ሙያ ያሰማራቸውን አስመልክተውም ይህንኑ ለመሸፍን በጎረቤት ሀገር አመፀ በማሳበብ በፊላ ዉሃ ለማርገብ ሞከረ ሲሉ ገልጸውታል።

ሴናተር ፌንጎልድ በንግግራቸው በኢትዮጵያ ያለው "ብልሹ አስተዳድር" እና "የሰብአዊ መብት ጥሰት" እጅጉን እንዳሳሰባቸዉ ተናግረዋል። በተለይ የሀገራቸዉ መሪ" ቡሽ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት አስመልክተው የተከትሉት መንገድ አርቆ አስተዋይነት የጉደለው እና ከጠባብ አስተሳሰብ የመነጨ" ውሳኔ መሆኑን አልሻሸጉም። የአሜሪካና የኢትዮጵያ ግንኙነት መመስረት የነበረበት አንድን ሰው ከመደገፍ ይልቅ በግልፅ ምን እየተፈጠረ ነው የሚለውን በማስተዋል መዋዕለ ንዋይ መመደብ ያለብን ለኢትዮጵያ ተቋማትና ለሕዝቡ የተረጋጋና የሰከነ የፖለቲካ ስርዓት የሚፈጥርበትን" ሁኔታ የሚያመቻች መሆን አለበት ብለዋል።

አሜሪካ በኢትዮጵያ ያላትን መሰረታዊ ፓሊሲ በተመለከተ ሴናተር ፌንጎልድ በትክክል ጉዳዩን ለይተውታል አንድን ሰው መደገፍ እና ከ80 ሚሊዮን ሕዝብ ጎን መቆም ብሎም የዴሞክራሲ ተቋማትን በማቋቋምና መልካም አስተዳድር እንዲሰፍን መርዳት በመጋቢት ሁለት የመረጃ መስሚያ ቀነ ቀጠሮ ለእነዚህ ጥያቄዎችና ሌሎች የሚመለከቱ ጉዳዮች ተይዞ ነበር።ችግሩን አስመልክቶ ሴናተር ፌንጉልድ በሰጡት ትንታኔ ላይ እንስማማለን መልሱ በአሜሪካ ላይ እንዳረፈ እናምናለን በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ እንዲኖርና መስረቱ የማይናጋ እንደሆን የሕግ የበላይንት በተቋም ደረጃ እንዲመሰረት በብርቱ እንጠይቃለን ሴናተር ፌንጉልድ ለማስረዳት እንደሞከሩት ኢትዮጵያ ዛሬ በአንድ ሰው ጭቆና ስር ወድቃለች የሕግ የበላይንት ተጥሷል።የቡሽ አስተዳደር በፀረ ሽብርተኝነት ዘመቻዉ የሰጠው ድጋፍ የአዲስ አበባው አገዛዝ በአፍሪካ ቀንድ የሕገወጥነት ባህል እንዲያድግ ህገወጥነት እንዲጎለብትና የሕግ የበላይንት እንዲረጋገጥ የዴሞክራሲ መርህ እንዲጣስ ያለምንም ጥያቄ አስተዋፆኦ አድርጉል።

ነገር ግን ለአሜሪካ አሁንም ጉዳዮን ወደ ተሻለ አቅጣጫ እንዲያመራ ለማድረግ ገና አልዘገየም በመሆኑም የአሜሪካን በኢትዮጵያ የምትከተለውን መርህ እንደገና እንድትጠይቅ አሜሪካ 80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሕግ የበላይንትን መሰረት ያደረገ ዴሞክራቲክ ስርዓት እንዲገነባ ለመርዳት። አሜሪካ የዴሞክራሲያዊ ሂደቱ እንዲገነባ በሚከተሉት ዘርፎች ላይ ትኩረት ትስጥ።

የፓለቲካ እስረኞችን በአስቸኳይ መፍታት

ወያኔ በመጀመሪያም ደረጃ መታስር የሌለባቸውን ንጹሀንን አስሮ በማጉላላት ከዚያም በመፍታት የፈለገውን የስነልቦና የበላይነት በፓለቲከኞች ላይ ሊያገኝ አልቻለም። የፓለቲካ እስረኞች ይፈቱ ማለት አስረው አሸናፊነቱን ለማሳመን በንፁሃን የፓለቲካ እስርኞች ላይ የፈለገውን ይፈጽም ማለት አይደለም። ይህንኑ የበላይነት ለማግኘት በሕግ ወጥ መንገድ አስገድዶ በቁጥጥር ስር ካዋላቸዉ በኃላም ጥፋተኛነታችሁን አምናችሁ የይቅርታ ሰነድ ፈርማችሁ ከእስር ትፈታላችሁ ማለት በምንም መስፈርት

ትክክለኛ የፓለቲካ እስርኞች አፈታት ዘዴ አይደለም። በዚሁ በተለመደው በሕግ ወጥ መንገድ በቁጥጥር ስር ያዋላቸዉን ሰባ ሁለቱን ዛሬ ለቆ፤ ከወር በኃላ ሰላሳ ስምንቱን እፈታልሁ ብሎ፤ በሌላው በር ደግሞ በየሳምንቱ በመቶ የሚቆጠሩትን ዜጎች ወደእስር ቤት ሲያስገባ በዚህ ዓይነት በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በሕግ ወጥ መንገድ በቁጥጥር ስር ማዋል ወያኔ በሕዝቡ ላይ የሚቀልደው ቀልድ የሚያስቅ ቀልድ አይደልም። ይህ አረመናዊ ቀልድ ቆሞ አሁኑኑ ያለምንም ቅደመ ሁኔታ ሁሉም በሃገሪቱ ውስጥ የታሰሩ የፓለቲካ እስረኞች ባስቸኳይ መፈታት እንዲችሉ ተከታታይ ፕሮግራም መኖር አለበት። አገዛዙ እራሱ ያቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን 30ሺህ የፓለቲካ እስረኞች በመዝገቡ በጥቂት ወራት ውስጥ አጣርቶ መያዙን አረጋግጧል። አሁንም ሌላ አጣሪ ኮሚሽን ተቋቋሞ ይህንኑ የማጣራት ተግባርም በአጭር ጊዜ የማይወጣበት ምክንያት የለም።

የሰብአዊ መብት የጣሱትን ለፍርድ ማቅረብ

በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብትን የጣሱ በርካታ ግልሰቦችና ባልስልጣናት አሉ።በ1997 ዓ፡ ም በሁለት የሰላማዊ ሰልፎች ብቻ 191 ንጹሀን ዜጎች መገደላቸውን የአጣሪ ኮምሽኑ አረጋግጦ ይሂአል።ሌሎች በሽህዎች የሚቆጠሩ የድብደባ፡የማዋከብ፡ ህገውጥ መጉላላት ሌሎችም ወንጀሎች የተፈጸሙባቸው አሉ።191 ንጹሀን ዜጎችን የገደሉት የታወቁ በመሆኑ በአስቸኳይ ለፍርድ መቅረብ አለባቸው።አገዛዙ ሰብአባዊ መብትን በመድፈር ጭፍጨፋ የፈጸሙ የደህንነትና ሌሎች ተጠርጣሪ ባለስልጣናትን በመሸፈን ከለላ ሊሆናቸው አይገባም።እነዚህ ሰቆቃ የፈጸሙ ሁሉ በተባበሩት መንግስታት በጽረ ሰቆቃ ድንጋጌ መሰረት ሳይዝግይ ለፍርድ ሊቀርቡ ይገባል።

ነጻ ምርጫ ዋስትና እንዲኖረው ነጻና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ ቦርድ ማቋቋም

ነፃና ገለልተኛ የምርጫ ተቋም በሌለበት እውነተኛና ትክክለኛ ምርጫ፡ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር፡ የሕግ የበላይነት በኢትዮጵያ ይኖራል ብሎ ማሰብ ዘበት ነው። በኢትዮጵያ የሚታየው ምርጫ ያሻንጉሊት ጨወታ ይመስላል። ጨወታውም ትክክለኛ ምርጫ አለ ብሎ ለማሳየት፤የምርጫ ሕግ ማውጣት፡ ለመራጭ ምዝገባ መዥዥጥ፡ የተወዳዳሪ ምልመላው፡ የፓርቲ ምዝገባው፡ የመገናኛ ብዙሃኑ ማስተጋባቱና ተፍተፉ የዕርዳታ ሰጪ አገሮችን ለማወናበድ እንጂ እውነተኛ ምርጫ ለማካሄድ አልነበረም።

ልክ እንደ ቁማር ተጫዋቾች ካርድ እያሳዩ መሸወድ አይነት በምርጫ ሂድቱም ዋናው የምርጫ ተዋናይ ካልፈቀደ በስተቀር የሚያሸንፍ የለም።በዚህ የማታለያ ምርጫ ዙሪያ የተኮለኮሉት ሁሉ ለዋናው ሰው ሽፋን ለመስጠት ለማምታታት የቆሙ ናቸው።በ1997 የሽፋን ጨዋታውን ከምርጫው ማግስት ጀምሮ አገዛዙ አግባብ የሆነ ምርጫ ለማካሄድ እንደማይችል አረጋግጧል።በተቃራኒው ግን ወከባን ዋናው የአሰራር መመሪያው አደረገው።

ተገቢና ስርዓት የጠበቀ የምርጫ ሂድት እንዲኖር አሜሪካ በግድ ድጋፍ ማድረግ አለባት።ግልጽነትና ሁሉን አቀፍ የምርጫ ሥረዓት እንዲኖር ከተፈለገ ገለልተኛ የሆነ የአስመራጭ ቦርድ ማቋቋም ወሳኝ ነው። ይህንንም በበላይነት የሚቆጣጠሩት፤ ከሁሉም ፓርቲዎች የተወከሉ አባላት፣ባለሙያ የመንግሥት ሰራተኞች ፣ ቢመደቡ ሥራውን ግልጽና የተቀላጠፈ ያደርገዋል።ከዚህም በላይ ሌላው ጠቃሚ ጉዳይ የምርጫ አግባብነትና ነጻ ምርጫ እንዲኖር በተቋም ደረጃ ማዋቀር ያስፈልጋል። እንደዚሁም የብዙሀን ማህበራት ሕዝብን በማድራጀት፣ ስለድምፅ አሰጣጥ በማስተማር፣ መረጃ በማቅረብ፣ምዝገባ በማስፈጽም ሥልጠናን በመስጠት ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። በአሁኑ ወቅት የወያኔ መሪዎች የተደራጀን ሲቪሉ ሕዝብ እንደወንጀለኛ ቆጥረው ሲያወግዙ ሲበታትኑት ለውደፊቱ አግባብ ያለውና ነጻ ምርጫ ለማካሄድ አስቸጋሪ መሆን ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ እውነተኛ ዴሞክራሲ ለማምጣት ያስቸግራል።

ገለልተኛ የሆነ የዳኝነት አገልግሎት

በኢትዮጵያ ነጻ የሆነ የህግ ተቋም መኖር ያለአድሎ ሁሉም ዜጎች በእኩልነት የሚዳኙበት ሁኔታ ይፈጥራል። ያለፉት ሁለት አመታት በትቃዋሚ መሪዎች ላይ የታየው የፍርድ ሂደት በማንኛውም

መስፈርት ዳኞችና ፍርድ ቤቶች የፓለቲካ ተቃዋሚዎችን ወይም የተለየ መንገድ የመረጡትን ለመቅጫ መገልገያ መሣሪያ መዋል አልነበረባቸውም። አሜሪካ የፍርድ ሥረዓቱና የዳኝነት አገልግሎቱ በኢትዮጵያ እንዲሻሻልና ገለልተኛ እንዲሆን የምትጠይቅበትና የምትረዳበት አቋም ላይ ነች። ፍርድ ቤቶች የፍርድ ስርዓታቸውን እንደሕጉ ከሆነ ከማንም የወያኔ አገልጋይ ጣልቃ ገብነትና ማወናበድ እና ዳኞች ከፍረሃትና መሸማቀቅ ነፃ ሆነው በገለልተኛነት የዳኝነት ሃላፊነታቸውን መወጣት ነበረባቸው። በተጨማሪም የቀረበላቸውን ማንኛውንም አወዛጋቢ ጉዳይ በጥንቃቄ መርምረው ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ውሳኔያቸውን እንዲሰጡ መደረግ ነበረበት።

ከቁጥጥር የነፃና ገለልተኛ የሆነ መገናኛ ብዙሃን ማቋቋም

ነጻ ፕሬስ የተረጋጋ፣ጠንካራና ጤናማ ዴሞክራሲ ስርዓት እንዲኖር በጣም አስፈላጊ ነው።ከዚህ ውጭ በኢትዮጵያ መልካም አስተዳደር፣ ተጠያቂነት ያለው መንግሥት ፣የዲሞክራሲ እድገት ይመጣል ብሎ ማሰብ ተጨባጭነት የሌለው ብዥታ ነው።በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃንን አስመልክቶ ጋዜጠኞችን የሚካባከብ ደርጅት በ2000 ዓ ም ባቀረበው ዘገባ "የዘጠና ሰባቱን ምርጫ አስመልክቶ መንግሥት ባደረገው አፈናና ግድያ አስራ አምስት ጋዜጠኞች የእስሩ ሰለባ ሲሆኑ ብዙ ጋዜጣዎችም ከህትመት ታግደዋል። ይህ በነፃው መገናኛ ብዙሃን ላይ ያንዣበበው ግደባ እስከ 1999 ዓ ም ቀጥሏል"። ይሄው የጋዜጠኞች ተከባካቢ ድርጅት በደረሰው ድምዳሜ መሠረት አሁንም ቢሆን "በኢትዮጵያ የሚደረገው እስርና ወከባ ባለመቆሙ ብዙ እውቅ ጋዜጤኞች ለስደት መዳረጋቸውን" ገልጿል። በተጨማሪም ወያኔ ጋዜጠኞችን በማሰቃየት በዓለም ውስጥ ከታወቀችው ከዝምባብዌ ቀጥሎ መመደቡን ጠቁሟል። በቅርቡም የአልቡደስ ጋዜጣ አዘጋጅ ኢዘዲን ሙሐመድ፣ የአልቅዱስ አሳታሚው ማሪያ ካዲምና የሴሌፊያ አዘጋጅ ኢብራሂም ሙሐመድ ፡ ክስ ሳይመሰረትባቸው ወህኒ ወርደዋል።

ይህን መሰል መረን የለቀቀ ዘግናኝና አሰቃቂ ተግባር ወያኔ ገለልተኛ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ጋዜጦኞች ላይ ለዘመናት መፈጸሙ በኃይል ጸጥ ለጥ አድርጌ በሚስጢር አስተዳድራለሁ ብሎ ከማመን የመነጨ ከንቱ ውዳሴ ነው ። የዲሞክራሲ መሰረታዊ መርህ አስቀድመው እንደመሰላቸው ይዘውታል።ዜጎች መንግስት የሚፈጽመውን የማወቅ መብት አላቸው ይላሉ።የመጠየቅና የቀረጥ ገንዘብ በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን፤ በሥልጣን የባለጉ፡ የሕዝብ ንብረት ያባከኑ ካሉ የሚታወቅበት እና የሚያረጋግጡበት አንደኛው መንገድ ነው። የነፃው መገናኛ ብዙሃንም በማንኛው ሥፍራ እገባ ዜጎች ማወቅ የሚገባቸውን ሁሉ ሲያሳውቅ፡ ያላግባብ ሥልጣናቸውን የሚጠቀሙትን በማጋለጥ፡ ተመራጮች የተመረጡበትን በትጋት መሥራታቸውን፤ በግብር የተሰበሰበው ገንዘብ በስርት ስራ ላይ መዋሉንና ሕዝብ ያጉላሉትን ብሎም በሙስና የተዘፈቁትንና ሕግ የጣሱትን በሙሉ ለሕዝብ ያጋልጣል።

የአዲስ አበባው መሪዎች በምስጢር መሥራት የተጸናወታቸው ማንኛውንም ሐቅ ከሕዝብ ሰውረው ሌላው ቀርቶ ከውጭ የሚተላለፉት ዜናዎችን አፍነው ሕዝቡ ምንም አይነት የፓለቲካ መረጃ ከሃገር ውስጥም ሆነ ከውጭ እንዳያገኝ እየጣሩ ናቸው። የአሜሪካ ድምፅ የሚተላለፈውን ዜና ለሕዝቡ በትክክል እንዳይደርስ አፈና እየፈጸሙበት ይገኛሉ። የአሜሪካኑም የመማክርት አባል ሩስ ፌንጎልድ አጥብቀውም ወያኔን አውግዘው ሌሎችም የእርሳቸውን ፈለግ እንዲከተሉ የሚገፋፉትም ለዚህ ነው።የወያኔ መንግሥት ግን ከዚህ እኩይ ተግባሩ ፍንክች አላለም።

የመከላከያ ኃይሉን ከፓለተካ ገለልተኛ ማድረግ

የአሜሪካ መንግሥት ለኢትዮጵያ ጦር ኃይል ማጠናከሪያ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ መለገሱ አይካድም። ያም ሆኖ ግን በእርዳታው ገንዘብ የተገዛው መሣሪያ የተቃዎሚ ፓለቲካ አባላትን ለማንበርከኪያ መዋሉን የአሜሪካ መንግሥት በተገቢው ጥያቄ አላቀረበም። ሴናተር ፌንጎልድም አጉልተው ለማሳየት የፈለጉት በተለይ ከአሜሪካ በተገኘ የልገሣ መሣሪያ የኦጋዴን ሕዝብ መጨፍጨፉ የለበትም። እንደዚሁም የጦር መሳሪያ አላግባብ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም ባይ ናቸው።"የኦጋዴን ሕዝብ በልማቱ መስከ በመረሳቱ ቢያምጽ የወያኔ መንግሥት በአክራሪነት የመፈረጁ አዝማሚያና የከፋ ወታደራዊ

**እርምጃ በመውሰድ ለመደምሰስ መጣሩ በቅርብ እየታየ ያለ ጉዳይ ነው" የአሜሪካ መንግስት ወታድራዊ እርዳታው "በጨካኝ" ጨቋኞች አማካኝነት ሰላማዊ ተቃዋሚዎችንና ነዋሪዎችን አላግባብ መጨፍጨፊያ እንዳይውል መቆጣጠር አለበት።በእርግጥም የአሜሪካ የውጭ ወታድራዊ እርዳታ በምንም መልኩ የሰብአዊ መብትን የሚጥሱ መገልገያ መሆን የለበትም። በአሜሪካ ወታደራዊ እርዳታ መመሪያ መሰረት የኢትዮጵያ ፖሊስና ወታደራዊ ሀይል የአሜሪካን የእርዳታ መሳሪያ ተጠቅመው የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ለመጭቆኛ መጠቀሚያ ማድረግ የለበትም።**

**እንደምናምነው የመጋቢት** 2 **ቀን** 2000 **ዓ.ም የምክር ቤቱ የመረጃ ማዳመጥ የውይይቱ ስብሰባ መጨረሻው** H.R.2003 **በውሳኔ የሚያልፍበት ይሆናል።ከሁሉ በላይ በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲ፡ ነጻነት፡ ሰብአዊ መብት እንዲጎልብትና የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ** H.R.2003 **እንዲደግፉና ተገኝተው እንዲከታተሉ ጥሪ አድርገዋል።ያም ሆነ ይህ መጋቢት** 2 **ቀን** 2000 **ዓ ም በመማክርቱ ሸንጎ** H. R 2003 **አስመልክቶ በሚደረገው የመረጃ ማዳመጥ ስብሰባ ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በምክር ቤቱ በመገኘት መከታተል ይኖርብናል። ይህ** H.R 2003 **ሕግ ሆኖ ከጸደቀ በዝርዝር ስንገልፃቸው የነበሩትን የዲሞክራሲ፣ የነፃነት፣የሰባዊ መብትና የሕግ የባላይነትን ለማጎናጽ በር ከፋች ይሆናል።**